# የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘም ወይም ዘግይቶ የሚቀርብ የይግባኝ ማመልከቻ የሚስተናገድበት ስርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 106/2014

Guidelines Issued to Determine the System for Handling Late Appeals or Extensions of Time for Filing Appeals
(Directive No. 106/2014)

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን
Addis Ababa City Administration Tax Appeal Commission

ጥር 18፥ 2015

## ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜን ስለማራዘም ወይም ዘግይቶ የሚቀርብ የይግባኝ ማመልከቻ የሚስተናገድበት ስርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 106/2014

በታክስ አስተዳደር አዋጅ እና በማቋቋሚያ ደንብ ኮሚሽኑ አጥጋቢ ምክንያት መኖሩን ሲያምን የይግባኝ መቅረቢያ ጊዜ ሊያራዝም እንደሚችል የተደነገገውን በተመለከተ በተለያዩ ምክንያቶች ዘግይቶ የሚቀርብ የይግባኝ ማመልከቻ የሚስተናገድበት ስርዓት እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ደንብ ቁጥር 105/2011 አንቀፅ 19 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ኮሚሽኑ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭርርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘም ወይም ዘግይቶ የሚቀርብ የይግባኝ ማመልከቻ የሚስተናገድበት ስርዓት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 106/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

   1. ‹‹አዋጅ›› ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፣
   2. ‹‹ደንብ›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 105/2011 ነው፡፡
   3. ‹‹ኮሚሽን›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ነው፡፡
   4. ‹‹ፕሬዚዳንት›› ማለት የኮሚሽኑ ፕሬዝዳንት ነው፣
   5. ‹‹የኮሚሽኑ ችሎት ዳኞች›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን የችሎት ዳኞች ነው፣
   6. ‹‹ሬጅስትራር›› ማለት የኮሚሽኑ ሬጅስትራርና የችሎት ዳይሬክቶሬት ማለት ነው፣
   7. ‹‹ውሳኔ›› ማለት የኮሚሽኑ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ ነው፣
   8. ‹‹መልስ ሰጪ›› ማለት እንደአግባብነቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸዉ፡
   9. ‹‹ይግባኝ›› ማለት በመልስ ሰጪ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ይግባኝ አቤቱታ ነው፣

10. ‹‹ይግባኝ ባይ›› ማለት በመልስ ሰጪ በተሰጠው ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ የይግባኝ አቤቱታ ለኮሚሽኑ ያቀረበ ሰው ነው፣
11. ‹‹ዘግይቶ የቀረበ ይግባኝ›› ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀፅ 88(1) መሰረት ይግባኝ ሊቀርብበት በሚገባው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልቀረበ የይግባኝ አቤቱታ ነው፡፡
12. ‹‹ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው እንዲረዘም የሚቀርብ አቤቱታ›› ማለት ይግባኝ የማለት መብት ያለው ሰው ይግባኝ የሚቀርብበት ጊዜ ከማለፉ በፊት ይግባኝ ለማቅረብ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው የሚቀርብ አቤቱታ ነው፡፡
13. በታክስ አስተዳደር አዋጅ፣ በጉምሩክ አዋጅ እና በገቢ ግብር አዋጅ እና በኮሚሽኑ ማቋቋሚያ ደንብ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረግ ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ለኮሚሽኑ ዘግይተው በሚቀርቡ ወይም ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜያቸው እንዲራዘም በሚጠየቁ የይግባኝ አቤቱታዎች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን ስለማራዘም እና ዘግይቶ ስለሚቀርብ ይግባኝ

4. **የይግባኝ ማቅረቢያ**

1. ይግባኝ ባይ ወይም ወኪሉ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ከማለፉ በፊት ይግባኝ የማቅረቢያ ጊዜው እንዲራዘምለት በፅሁፍ ለኮሚሽኑ ፕሬዝዳንት ሊያመለክት ይችላል፣
2. ይግባኝ ባይ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ እንዲራዘምለት ጥያቄውን ሲያቀርብ ምክንያታዊ ያልሆነ መዘግየት ያለመኖሩን እና እንዲራዘም የፈለገበትን ምክንያት በማመልከቻው መግለፅ እና ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፣

5. **የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜን ስለማራዘም**

ኮሚሽኑ በዚሁ መመሪያ አንቀፅ 4 መሰረት የቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር ይግባኝ ባዩ ይግባኙን ያላቀረበው ከአቅም በላይ ወይም አሳማኝ በሆነ ምክንያት መሆኑን ሲያምንበት የይግባኝ ማቅረቢውን ጊዜ የይግባኝ ማቅረቢያው ቀን ካበቃበት ቀን ጀምሮ ከ15 ቀን ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

6. **ዘግይቶ ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. ዘግይቶ ለሚቀርብ ይግባኝ በቅድሚያ የዘገየ ይግባኝ ይከፈትልኝ አቤቱታ ማቅረብ አለበት፡፡

2. በአቤቱታው ይግባኙ በጊዜው ሊቀርብ ያልቻለበትን ምክንያት እና አሉኝ የሚላቸውን ማስረጃዎች በዝርዝር ማቅረብ አለበት፣

7. **ዘግይቶ የቀረበ ይግባኝ የሚስተናገድበት ስነ ስርዓት**

1. ኮሚሽኑ አቤቱታው በደረሰው በሶስት ቀናት ውስጥ መልስ ሰጭ በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ይላክለታል፡፡
2. መልስ ሰጭ አስተያየት የሚሰጥ ከሆነ በፅሁፍ ማቅረብ አለበት፣
3. መልስ ሰጪ አስተያየት ከሰጠ በኃላ ወይም አስተያየቱን በተወሰነው ቀን ገደብ ካላቀረበ ኮሚሽኑ በቀረበው አቤቱታ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. ዘግይቶ የቀረበዉን ይግባኝ ተቀባይነት ለመወሰን ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ በችሎት ክርክሩን ሊሰማ ይችላል፡፡

8. **ዘግይቶ የሚቀርብ ይግባኝን ስለመፍቀድ**

1. ኮሚሽኑ በአቤቱታ ላይ የተገለፀው ምክንያት በፍትሐብሄር ህግ አንቀፅ 1793 ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ተብሎ የተገለፀውን ሁኔታዎች ያሚላ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ለተመለከቱት ምክንያቶች በቂና አሳማኝ ማስረጃ አግባብ ካለው አካል መቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1 እና 2) የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአቅም በላይ የሆኑ ሌሎች ምክንያቶችም በቂና አሳማኝ ማስረጃ አግባብ ካለው አካል ከቀረበ ኮሚሽኑ ይግባኙ እንዲቀርብ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ይግባኙን እንዲያቀርብ ይፈቅድለታል፡፡
4. ይግባኙ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ኮሚሽኑ በወሰነ ጊዜ ውሳኔው ላይ ይግባኝ ባዩ እና መልስ ሰጭ በፅሁፍ እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

9. **ተፈፃሚነት የማይኖራቸው አሰራሮች**

ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አሰራር ወይም መመሪያ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

10. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፕሬዝዳንቱ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር 1 ቀን 2014 ዓ.ም

ታረቀኝ አስፋው ከበደ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዝዳንት